ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በ ጥር 29 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# የሰጎን ፖለቲካ ከውድቀት አያድንም

ፖለቲካ በየዓይነቱ ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል ። ብዙዎቹ ጨፍረውብታል ። ሹሙ የሰጎንና የዲስኩር ፖለቲካ ምሩቅ ነው ። የራሱ ሀቅና ተጨባጭ ሁኔታ አለው--የሕዝብ አይደለም ወይም እውነትም አይደለም ። የሰጎን ፖለቲካ የሚባለው አፍጦና ደጀን ተራራን አክሎ ያለውን ሀቅና ተጨባጭ ሁኔታ አላይም አልቀበልም ማለትን--ቅጥፈትን ልንለውም እንችላለን- በግልባጩና በሚገባው ስያሜ-ማራገብን ይመለከታል ። ሰጎን አንገቷን በአሸዋ ውስጥ ስትቀብር አዳኞቿ የሚያዩአት አይመስላትም ።መጨረሻዋም ሞት ምሆኑ ግልጽ ነው ።

ሹሙ ከሰጎን ሰጎን የሆነው በሀገራችን የተከሰተውን--ያስከሰተውን አስከፊ ሁኔታ--የለም ብሎ በሕልም ይጋልባል ። ዕቅዱ ህዝብን ለማደናገር መሆኑ ደግሞ ሸሩን የከፋ ያድርገዋል ። ታከለ ኡማን ዓይነቱን የለየለት ዘረኛ ሾሞ አዲስ አበባን ለመቆጣጠር መጣር በጣም ያስገምታል ። ዜጎች እኮ በጠራ ዓይናቸው እነማን እንደሚሾሙ እነማን ጥቃት እንደሚደርስባቸውና ሊደርስባቸውም እንደታጩ ያውቃሉ ። ባለሜንጫውን ያቀፉት ሹሞቹ ናቸው ።ታምራት ላይኔን የክብር እንግዳ በሚል በሀይማኖታቸው ማጠየቂያ (ዘመነ ፓስተሮች) ያቀፉት ሹሞቹ ናቸው ።የሕዝብን ቅሬታ አናይም አንሰማም ብለዋል ። ወደ ውሸት ሲመጣም ለኢሳያስ የሰገደው ሹም ሸምጥጥ አድርጎ እንደሚዋሽ ስናጋልጥ ቆይተናል ። ከሀቅ ተጣልቷል ተጋጭቷል ብዙ ጊዜ ። በቅርቡ ባደረገው ንንግር ለምሳሌ ማንም "ሚዲያ በውጭ ሀገር የለም ፡ሲል ተደምጧል ። ወደ 20 ድርጅቶችም ሲገቡ አንድም በውጭ ህገር አልደግፍም ያለ የልም ሲል ቀጥፏል ። የሰጎን ፖለቲካ ። ሹሙና አለቆቹ ኢሕአፓ በተቃዋሚነት እንዳለ፤ፍኖተ ዴሞክራሲ ከውጪ እንጂ ከአዲስ አበባ እንደማያስተላልፍ ጠንቅቀው ያውቃሉ ። ሊከሱን፤ሌጉን፤የሉም ሊሉንም እስካሁን በመፍጨርጨር ላይ መሆናቸው ምስጢር አይደለም ። 40 ዓመት የሆናቸው ድርጅቶች ሳይቀሩ ተደባለቁኝ ሲል ከኢሕ አፓ ሌላ 40 ዓመት ያስቆጠረ ድርጅት አለመኖሩን ስናውቅ አንጃን ያው ለማጭበርበር ኢህ አፓ ማለቱን ለመድገም ነው ማለት ነው ። ሹሙ የአሜሪካኖችን ጻረ ኢሕአፓነት መውረሱን የሚያረጋግጥ ልፈፋ ነው ። ሹሙ ላገኛቸው ተደማሪዎች በምስጢር ሲለፍፍ የሕዝቡን ትግል መርተን እዚህ አድረስነው ማለቱን እናውቃለን ። አላሉም አክለን እንረታዋለን ።ያለው ግን ውሸት ነው ።ትግሉን እዚህ ያደረሰውን ወያኔን ያዳከመው ደሙን ያፈሰሰውና ተባብሮ ወያኔን የተጋተረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ። የሕዝብን ስራና ድምጽ መንጠቅ ወንጀል ነው ። ከክቡር ሊቀመንበር ሌላ ማን ምን ሰርቶ ትላንት? ከግብዙ መለስ በላይ ብልህ መች ተደምጦ?

ሹሙ የሽግግር ሂደቱን ህጋዊ ተግባሮች ሰርዞ በራሱ ሁሉን ወሳኝ ሆኖ ሲቧርቅ ሰፊው ሕዝብ መቃወሙን ባይናገሩትም አዳምጠውታል ። ሰውየው ተቃዋሚ የተባሉ አድርባዮችን ሆነ መላ ሕዝቡንም ንቆ ይገኛል ። የምርጫ ቦርድን ሃላፊ ማን ሳይሆን እሱ ያው በእምነት ማጠየቂያ ሾሞ ይገኛል ። የድንበር የዕርቅ ኮሚቴ ሲል እንኳን ፓርላማ ተብዬውን ራሳቸውን ተሿሚዎችንም አስቀድሞ እንዳላማከረ እየሰማን ነው ። ለእርቅ ኮሚቴ እነማን ተሾሙ? የሲዳማ ሕብን ፈጆ የሚባለው ለፍርድ ይቅረብ የሚባለውን የመለስ መጋዣ የተባለውን ሀይለማርያም ደሳለኝን መድቦታል ። ብዙዎቹ ጥያቄ የተነሳባቸውና ራሳቸው ዕርቅ አምጪ ሳይሆኑ ዕርቅ ጠያቂም የሆኑ ናቸው ። ከወንጌላውያን ሁለት ሰው ሲመደብ ከኦርቶዶክስና

ሙስሊሞች ወካይና የሚከበር የተባለ ማንም አልተመደበም ። ጥያቄ ያለባቸው ፖለቲከኞችና ምሁሮች አስታራቂ ሊሆኑ የሞራል ብቃትም ተቀባይነትም ባይኖራቸውም ያው ለሹሙ ስላመቹ በሹሙ ተመድበዋል ። የኪነ ጥበብ ሰዎችንስ ወካይ ራሱን በተደጋጋሚ ያጋለጠው ደበብ እሸቱ ነው ? ሹሙ በይፋ ቀልዷል ። ምሁራን የተባሉትም በጣም አነጋጋሪ ናቸው። ወያኔው አባተ ኪሾ እንዴትስ የሲዳማ ሽማግሌዎች ተወካይና አስታራቂ ይባላል? ግደይ ዘርአ ጽዮን (የወያኔ መስራችና አሁንም ወልቃይት የወያኔ ነው ባይ )ና መሰሎቹ እንኳን አስታራቂ ሊሆኑ ከሕዝብ የሚያስታርቃቸው ፈላጊ ናቸው ።በዚህ ይዘት መቀጠል እንችላለን ። ዋናው ግን ወያኔ መሬት ሲሰርቅ ያልተነፈሱ፤ሱዳን ሀገር ሲወር አንገታቸውን የቀበሩ ና ለሹሙና ወያኔ የሚያመቹ መሾማቸውም በጥያቄ የሚገባ ነው ። ለዕርቅ ኮሚቴ መርጦ መስራች  ሹሞቹ ሳይሆኑ የሽግግር ሂደትና መንግሥት መሆናቸውን እንደሚገባ እኛ አልሳትንም ። በድንበር ኮሚቴም እንዲሁ የሕዝብን ማንነት የካዱ፤ ወያኔ መሬት ሲሰርቅ ቅንጣትም ያልተነፈሱ፤ሱዳን መሬታችንን ሲይዝ አልሰማንም ያሉ መመደባቸው የሹሞቹን ከንቱነት አጋልጧል ። ገዢዎች የሚያናፍሱትን የሰጎን ፖለቲካ ሕዝብ ራሱም ካቀፈው ግን ይብላኝ ለሀገር የሚያሰኝ ነው ። በጊዜና በጠዋቱ ተከለውሰነቱ የተናፈሰን ሹምና አገዛዝ ይዘት በሃቅ ስናጋልጥ፤ ከማውገዝ ይልቅ ማዳመጡ ለሀገር ይጠቅማል ብለን ነበር፤አሁንም  እንላለን ። ልጓም ለቆ ቼ ቼ፤በመንጋ ጫጫታ መጭ ማለቱ ሀገር ያጠፋል፤ያስጠፋል፤ለዘረኞች ሁሉም ያመቻል ።

ለምን ስንታገልና ደም ስንገብር እንደቆየን አስታዋሽ ፈላጊም ልንሆን አንችልም ።ሀቁን ለመናገር የትግላችንን መነሻና ግብ ልንረሳ ከቶም አይፈቀድም ። አዎ አይፈቀድም--ይህማ ጫኑን ጋልቡን ይሆንብናል ። ኢሕአዴግን በመቃወም ወያኔን ከዚህ ግሳንግሱ ለመጣል ነው ሕዝብ የታገለው ። ሹሙ ደግሞ የለም ይህ ሀቅ አይደለም ፤ወያኔን የታገልነው እኔና ጓደኞቼ ነን፤ የታገልነውም ኢሕአዴግን ለማሰቀጠል ነው ብሎ በይፋ ነግሮናል ። ይህ ሀሰት መሆኑን፤ ጸረ ሕዝብም አቅዋም መሆኑን ወዳጆቹ የተባሉትም ዛሬ በይፋ እየተናገሩት ነው ። የራሱን ብሄር የበላይነት ማስፈኑን ሁሉም ሊታዘብ ችሏል ። ባለለሜንጫዎችና አማራ ይጥፋ ባዮችን አቅፎ  ወደ ሀገር አንድነትና ወደ ለውጥ ይወስደናል ብሎ ማሰቡ ቅዠት ነው ። ሹሙ የኦሮርሞ ጠባቦችን፤የደርግ ወንጀለኞችን፤የሀይማኖቱን ተከታዮችን በመሰብሰብ ላይ ነው ። ነጻውን ሲኖዶስ ተብትቦ ከጥቅም ውጪ አድርጓል ።ታጋይ ሙስሊሞችን ጥግ አስይዟል። ሀገር ወዳዶችንም አግልሏል ።ኢትዮጵያዊነትን አዳክሟል ። መዋጥ ያለበት ኮስ ኮሶ የሚለው ሀቅ ይህ ነው ። በርካታ ሀገራቸውን የሚወዱ ወጣቶች የግርግሩና የጫጫታው ሰለባ ሆነው ሲታዩ ያሳዝናል ። ነገ ያሰቡት ሳይሆንና ዳግም በጮሌ ፖለቲከኞች ሰለባ ሲሆኑ ሞራላቸው መውደቁን ከወዲሁ መገመትና የሚከተለውንም ጉዳት መገመት እንችላለን ። በአድነነ ደረጃ የሚወገድ ሳይሆን ዘመቻና ገለጻንም ፈላጊ ነው ። ወጣቱ ስለ ሀገሩ በጥልቀት ማወቅና ያለውን ተጭባጭ ሁኔታ ከስሚታዊ ና ግልብ ግምገማ ውጪ መገንዘብ መቻል አለበት ። ሹሞቹም ህልው የሆነና ያለን ድርጅት፤ሕዝብ በስፋት የሚዳምጠውን ፍኖተ ራዲዮ የሉም ብሎ አንገት መቅበሩ  የሚያዋጣቸው አይሆንም ። ትግል ይቀጥላል፤ወደዱ ጠሉም ቀኑን ቆጥሮ ሕዝብ ይነሳባቸዋል።ውድቀታቸውም አስከፊ ይሆናል ። ወያኔ ገና 50 ዓመት ሊገዛን አስቦ ነበር ። ደርግም ዘለዓለማዊ ነኝ ሊል ከጅሎት ነበር ። ሁሉስ የት ናቸው ዛሬ? ለወያኔዎች መቸ ጠፋችላቸውና ነው፤ ሹሙ ዘረኝነትን አስቀጥሎ ኢትዮጵያዊነትን ሊያጠፋ ያሴረው?

የሰጎን ፖለቲካ የሀሰት ፖለቲካ ከመሆኑ ባሻገር በአሁኑ ጊዜ የፋራዎች ፖለቲካ ነው ። በሬ ሆይ በሬ ሆይ፤ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ ፖለቲካ ። ሕዝብን አደናግሮ መግዣ ።ለምሳሌ ዕርቅ ከኤርትራ የተባለው የራሳቸውንም ፓርላማ ሆነ ደሙንን ያፈሠሰውን ሕዝብ ከቶም ያላማከረ ፖለቲካ ጥቅሙ (ላም አለኝ በሰማይ ጅልነት ሲደረደር) ጉዳቱ መቸም አይቀርብም ።

ጸረ ኢትዮጵያው ኢሳያስ ግቡ ምንድነው ብሎ መጠየቅ ራሱ ሐጢያት ሊባል ትንሽ ቀርቶታል ። ይህ ዓይነቱ ጭፍን ፖለቲካ ሀገራችንን እንደሚጎዳ ጥርጥር የለውም ።ኢትዮጵይ ለአረቦች መጋለጧም ራሱ ከባድ ጉዳት የሚያስከትልብን ይሆናል ።አየር መንግዱን ለአረአቦችና ለባዕዳን ለመሸጥ የተሞከረውም ጥቅሙ የሚታይ አይደለም ። ለሻዕቢያም በከሳ መልክ ሊሰጥ የታሰበውን ገንዘብና ንብረት ሕዝብ ፈቅዷል?

ሹሙ በተጨባጭ በኢሕአፓ ላይ ያለው ጥላቻ ያው ከረጅም ዓመታት ብሄርተኛትና ወያኔነት ጋር የተያያዘ ነው ። አሜሪካም ድርጅቱ አክራሪ ኢትዮጵያዊ ነው ብሎ ስለገመገመ (ሹሙ ከመሾሙ በፊት የቀረቡትን የጥናት ሰነዶች ያጤኗል) ከሂደቱ ተግልሎና ተወግዶ ይቆይ የሚለውን ዕዝም ለሹሙ ስለሰጠው ነው ። የራሱ የደህንነት የምርመራ ተቋሞች አንጃና ኢሕአፓ ለየቅል ናቸው ሲሉ ወደ አሜሪካ ከመጓዙ በፊት ጥናት ሰጥተውት እንደነበርም እናውቃለን ። ጥላቻ ስሜት ነው-- ብዙውን ጊዜም የከፋ ሊሆንና ለተሳሳት ድምዳሜን አጋላጭ ሊሆን ይችላል ። ሹሙ በራሱ አለስልጣኑ ለዕርቅና ለድንበር ኮሚቴውች የሰየማቸው ብዙዎቹ ለቦታው የማይሆኑ፤አንዳንዶቹም ችሎታ አልባ የሆኑ፤ሌሎችም ለኢትዮጵያ ያልበጁና ሲጎዷትም የከረሙ ናቸው ። ህዝብን አላዳምጥ ብለው፤ ተጨባጭ ሁኔታውን በሰንናዊ አንገት ቀበራ ሸኘተው ወደፊት የሚሉት ጫጫታ፤ ወደ ኋላ እሪታን እያስከተለ ነው ። ኢትዮጵያ ከዓመት በፊት፤ የሕዝቧ ትግልና አንድነት ከዓመት በፊትና ዛሬ ጋር ሲነጻጸር ይበልጥ መበላሸቱን ማንም ኢትዮጵያዊ (ባንዳ፤ከሃዲና ጸረ ኢትዮጵያኖች በቀር) የሚገነዘበው ነው ። ሹሞቹ ኢትዮጵያ ላይ መርገም ናቸው ። የነገ እቅዳቸው ደግሞ ዘረኝነትን አንግሰው ሕዝብን አፋጅተው የጠባብ ግንጠላ ግባቸውን እውን ለማድረግ ነው ። ጥቅም ያልገዛውና ያልታወረ ይህንን ማየት መረዳት አያቅተውም ።

ኢሕአፓና ፍኖተ ራዲዮ ህልውናቸው ጠብቀው ለኢትዮጵያ የታገሉ ናቸው ። ሹሞቹ እርም ያውጡ። የሕዝብ ድጋፍ ከቶም አይለየንና ኢትዮጵያን ከጥፋት እናድን ነው መልእክታቸው ።

ጸረ ወያኔ ጸረ ኢሕአዴግ ትግላችንን ተፋፍሞ ይቀጥል !!

ኢትዮጵያዊነት ያቸንፋል !!

ዕርቅም ድንበር ጥበቃውም በሕዝባዊ መንግሥት !!